# በኢትዮጵያ ፡ ገንዘብን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋልን ፡ ለማበረታታት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶችን ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርገው ፡ ሕግ ፡

ከቲሞቲ ፡ ፒ ፡ ቦድማን ፡

## መግቢያ ።

ኢትዮጵያ ፡ ዕድገቷን ፡ ለማፋጠን ፡ ስትል ፡ ከአንድ ፡ ከተወሰነ ፡ ካፒታል ፡ በላይ የሚቋቋሙትን ፡ ድርጅቶች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርጋለች ።[1] የዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ እርምጃ ፡ የወሰደችው ፡ አገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ አይደለችም ። ብዙ ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አገሮችም ፡ ተመሳሳይ ፡ ሕጎች ፡ አሏቸው ።[2] የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ፡ በገቢ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ ማስቀረት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ እንደሚያስከትልና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተፈላጊ ፡ እንደሆነ ፡ መግለጽ ፡ ነው ። ጸሐፊው ፡ ለጽሑፉ ፡ የሚረዱትን ፡ በሜክሲኮና ፡[3] ፑዌርቶ ፡ ሪኮ፡ [4] የተደረጉትን ፡ ጥናቶች፡ በሰፊው ፡ ይጠቀምባቸዋል ። በማደግ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ አገሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጭምር ፡ የተደረገው ፡ ጥናት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የቆዩ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ከሚሰጡን ፡ አስተያየት ፡ በቀር ፡ ውይይታችን ፡ የሚመለከተው ፡ የሕጉን ፡ አደረጃጀት ፡ እንጂ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ አይደለም ።

## ፩/ ታሪክ ።

በመጀመሪያዎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ሕጎች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጉ ፡ ክፍሎች ፡ አልነበሩም ። እነዚህም ፡ ሕጎች ፡ የ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ. ም. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ እና ፡ የ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ. ም. ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፯ ፡ ናቸው ። በነዚህ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ በእርሻ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ አይከፈልም ፡ ነበር ። ሁኔታውም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡[5] ዓ. ም. ድረስ ፡ ሳይለወጥ ፡ ቆየ ። ቢሆንም ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆን ፡ ዕድል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ምናልባት ፡ ለአንዳንድ ፡ ድርጅቶች ፡ ቢሰጥም ፡ የኢንዱስትሪዎችን ፡ የመቋቋም ፡ እርምጃ ፡ ለማፋጠን ፡ ሲባል ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ማስቀረት ፡ ዘዴ ፡ በይፋ ፡ የተገለጸው ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አማካይነት ፡ በወጣ ፡ አንድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የማስታወቂያው ፡ ቃል ፡ በከፊል ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

> የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ለሀገሪቱ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ በታዩት ፡ ፕሮግራሞች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ካፒታል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠራ ፡

---

1 ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ቍጥር ፡ ፪፻፵፪/፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፪ ።

2 ኢንተርናሽናል ፡ ቼምበር ፡ ኦቭ ፡ ኮሜርስ ፤ ታክሴሽን ፡ ኦቭ ፡ ኢንካም ፡ ኦሪጂኔቲንግ ፡ ኢን ፡ ፕሮሴስ ፡ ኦቭ ፡ ዲቨለፕሜንት ፡ (፲፱፻፷) ።

3 ሮዝ ፡ ኤንዶ ፡ ክርስተንሰን ፤ ታክስ ፡ ኢንሴንቲቭስ ፡ ፎር ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ኢን ፡ ሜክሲኮ ፡ (፲፱፻፶፱) ። (ከአሁን ፡ በኋላ ፡ ሮዝ ፡ ኤንዶ ፡ ክርስተንሰን ፡ ተብሎ ፡ የሚጠቀስ) ።

4 ቴይለር ፤ ኢንዳስትሪ ፡ ታክስ ፡ ኤክዘምፕሽን ፡ ኢን ፡ ፒዮሪቶ ፡ ሪኮ ፡ (፲፱፻፶፯) ። (ከአሁን ፡ በኋላ ፡ ቴይለር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠቀስ) ።

5 አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፶፭ /፲፱፻፶፫ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳ኛ ፡ ዓመት ፤ ቍጥር ፡ ፬ ፡ ይህንን ፡ ነፃነት ፡ አስቀርቶታል ።

ለማበረታታት ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ የሥራ ፡ ዘዴ ፡ ወስኗል ። ይህንንም ፡ የሥራ ፡ ዘዴ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ መንግሥት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ካፒታል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለተጀመሩት ፡ አዲስ ፡ ፕሮጄዎች ፡ የተለዩ ፡ ጥቅሞች ፡ ለመስጠት ፡ ዝግጁ ፡ ነው ። ለውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ አግቢዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አኗኗራቸው ፡ እምነት ፡ ይሰጣሉ ፡ ተብለው ፡ የታሰቡት ፡ እነዚህ ፡ ጥቅሞች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።[6]

<u>፮/ ግብር ፤</u>

አዲስ ፡ ፕሮጄዎች ፡ ሥራው ፡ ከተጀመረበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ አምስት ፡ ዓመት፡ ድረስ ፡ ከጥቅም ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ይሆናሉ ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ማስታወቂያው ፡ ለፋብሪካው ፡ ሥራ ፡ መቋቋም ፡ "አስፈላጊ ፡ የሚሆኑት ፡ መኪናዎች ፡" ከውጭ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲገቡ ፡ ከጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ ነፃ ፡ እንዲሆኑ ፡ ቢወስንም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ በተመሠረቱት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ የሚለውን ፡ ሕግ ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ በመመልከት ፡ የሚሠራበት ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ ከተገኘው ፡ ትርፍ ፡ በከፊል ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መላክ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ ይደነግጋል ።

ማስታወቂያው ፡ የሚያገለግለው ፡ "ለሃገሪቱ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ በታዩት ፡ ፕሮጄዎች ፡" ላይ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህን ፡ አስተያየታዊ ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ ማን ፡ እንደሚያደርግ፡ አልተገለጸም ።[7] ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ እንዲሆኑ ፡ የታሰቡት ፡ አዲስ ፡ ፕሮጄዎች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ይህ ፡ ሰፊ ፡ አነጋገር ፡ የሚወሰንበት ፡ መንገድ ፡ በማስታወቂያው ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ በማስታወቂያው ፡ ውስጥ ፡ ከጉምሩክ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ስለ፡ መሆን ፡ የሚናገረው ፡ ክፍል ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርገውን ፡ ክፍል ፡ የሚያሻሽል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ከተነበበ ፡ አነጋገሩ ፡ ይጠባል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ከጉምሩክ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ስለመሆን ፡ የሚናገረው ፡ ክፍል ፡ ከግብር ፡ መክፈል ፡ ነፃ ፡ ያደረገው ፡ ለ"ፋብሪካው ፡" የሚጠቀሙትን ፡ መኪናዎች ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ስለመሆን ፡ የሚናገረው ፡ አንቀጽ ፡ "ፕሮጄዎች ፡" ሲል ፡ ፋብሪካዎችን ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ሊያሰኝ ፡ ይችላል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የአዋጁ ፡ ሰፊ ፡ አነጋገር ፡ እንደዚህ ፡ በጠባቡ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ፡ በሚል ፡ መንገድ ፡ በማስታወቂያው ፡ መግቢያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ "ለሀገሪቱ ፡ ጠቃሚ ፡ መስለው ፡ በታዩት ፡ ፕሮጄዎች ፡" የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ማስታወቂያው ፡ ፋብሪካዎችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎችንም ፡ ፕሮጄዎች ፡ ያጠቃልላል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

ማስታወቂያው ፡ የሚያሻማ ፡ ትርጓሜ ፡ የያዘበት ፡ ምክንያት ፡ "የሥራ ፡ ዘዴ ፡ መግለጫ ፡" እንጂ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ስላልወጣ ፡ ነው ። ማስታወቂያው ፡ ብቻውን ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ የነበረው ፡ አይመስልም ። የነበረው ፡ ሕጋዊ ፡ አስገዳጅነት ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩና ፡ ሌሎችም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሌሎች ፡ ሕጎች ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሥልጣን ፡ የሚጠቀሙበት ፡ "የሥራ ፡ ዘዴ ፡ መግለጫ" ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ ይመስላል ። ስለዚህ ፡ አቀራረቡ ፡ የግድ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ግልጽና ፡ የማያሻማ ፡ መሆን ፡ አልነበረበትም ።

---

6 የ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ-ም- ማስታወቂያ ፤ ቍጥር ፡ ፲ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ነኛ ፡ ዓመት ፤ ቍጥር ፡ ፮ ፤ ገጽ ፡ ፲፰፡ (፲፱፻፷፪) ።

7 ውሳኔው ፤ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ አስተያየት ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰጠ ፡ ይመስላል።

የዚህን ፡ ማስታወቂያ ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ቀጥሎ ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፵፱፡ ዓ. ም. የገቢ ፡ ግብር ፡ ድንጋጌ ፡ ነው ።[8] የዚሁ ፡ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ በግልጽ ፡ አኳኋን ፡ የ፲፱፻፵፱ን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይሽር ፡ እንደሚከተለው ፡ ደንግጓል ።

ከሁለት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ የኢት/ብር ፡ ባላነሰ ፡ ካፒታል ፡ የሚካሄድ ፡ የኢንዱስትሪ፥ የትራንስፖርትና ፡ የማዕድን ፡ ገቢ ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ ሥራ ፡ ከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ከአምስት ዓመት ፡ አይበልጥም ።

ድንጋጌው ፡ ይህን ፡ ዕድል ፡ ያገኙትን ፡ ሥራዎች ፡ ከመግለጹም ፡ በላይ ፡ ዕድሉን ፡ ሊያገኙ ፡ የሚችሉት ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በ፪፻ሺ ፡ የኢት/ብር ፡ የሚቋቋሙ ፡ ሥራዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጓል ። ሥራዎቹ ፡ ግን ፡ "አዲስ ፡ የተቋቋሙ ፡" መሆን ፡ አለባቸው ፡ የሚል ፡ ደንብ ፡ በድንጋጌው ፡ ውስጥ ፡ አልተጻፈም ። ስለዚህ ፡ በድንጋጌው ፡ መሠረት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የቆየ ፡ ድርጅት ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ድንጋጌው ፡ የ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ. ም. ማስታወቂያ ፡ ይበልጥ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ቢሆንም ፡ ቢያንስ ፡ በአንድ ፡ ረገድ ፡ ግልጽ አልነበረም ። ማስታወቂያው ፡ የአምስቱ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ መቆጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ሥራው ፡ "ውጤት ፡ ማሳየት ፡ ከጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡" ሲል ፡ ድንጋጌው ፡ ግን ፡ "ሥራው ፡ ከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላል" ። ስለዚህ ፡ የአምስት ፡ ዓመቱ ፡ ጊዜ፡ ሥራው ፡ ትርፍ ፡ ማግኘት ፡ ከጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የሚጀመር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ በመጠኑ ፡ ሊቀነስ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከድንጋጌው ፡ በላይ ፡ በመሆን ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡[9] ስለ ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ነው ። በአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ሥራ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ከ፪፻ሺ ፡ የኢ.ት ፡ ብር ፡ የማያንስ ፡ ካፒታል ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋሉት ፡ አዲስ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ የትራንስፖርትና ፡ የማዕድን ፡ ሥራዎች ፡ ሥራ ፡ ከጀመሩበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ይሆናሉ ። ስለ ዚህ ፡ ሕጉ ፡ የሚመለከተው ፡ "አዲስ ፡" ሥራን ፡ መሆኑንና ፡ በተጨማሪም ፡ ገንዘቡ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ መዋል ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ መሆኑን ፡ እንዲሁም ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ የሚቆጠረው ፡ ሥራ ፡ ከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቧል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የትርጉም ፡ ችግር፡ የሚፈጥሩ ፡ ቢሆኑም ፡ ከድንጋጌው ፡ ይበልጥ ፡ አዋጁ ፡ የተብራራ ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ።

በተጨማሪ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ (ሀ) ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ካፒታሉ ፡ ወጪ ፡ መደረጉን ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃና ፡ ሥራው ፡ መጀመሩን ፡ የሚያስረዳ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሥራው ፡ በተጀመረበት ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያዛል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ምርጫ ፡ አልተሰጠውም ። ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ የሚለው ፡ ሥራው ፡ "...ነፃ ፡ ይሆናል ፡"... ነው ፡[10] (እንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው)። ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ የሚያዘው ፡ ሁሉ ፡ ተሟልቶ ፡ ከተገኘ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

---

8 ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፮ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፩ ፤ ገጽ ፡ ፩ ፡ (፲፱፻፵፱) ።

9 የ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹፫ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ (፲፱፻፶፫) ።

10 ከዚያው ።

በአንቀጽ ፡ ፲፬(ለ) ፡ ደግሞ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በሚያቋቁመው ፡ ኮሚቴ ፡ በሚቀርብለት ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ "አንድ ፡ ተቋቁሞ ፡ ሥራውን ፡ በማካሄድ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፤ ሥራውን ፡ ለማስፋፋት ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ ያላነሰ ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ አድርጎ ፡ ..."[11] ሥራውን ፡ ሲቀጥል ፡ ያንን ፡ ሥራ ፡ "እስከ" አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ፡ (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ። ተጨማሪው ፡ ሥራ ፡ "ለብቻው ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ድርጅት ፡ ሆኖ ፡ የተለየም ፡ የሂሳብ ፡ መዝገብ፡ ይዞ ፡" መሥራት ፡ አለበት ። ከግብር ፡ ነፃ ፡ የሚደረገው ፡ አዲሱ ፡ "ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡" ብቻ ፡ ነው ። በ፲፬ (ሀ) ፡ የተደነገገው ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ በዚህ ፡ ጊዜም ፡ መፈጸም ፡ አለበት ። በ፲፬ (ለ) ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ ሚኒስትሩ ፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ የሚሰጠው ፡ በፈቃዱ ፡ ነበር ። ሚኒስትሩ ፡ ፈቃዱን ፡ የሚሰጠው ፡ አንድ ፡ ኮሚቴ ፡ በሚያቀርብለት ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ነው ። የግብሩንም፡ነፃነት ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ላነሰ ፡ ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻል ፡ ነበር ።

የአዋጁ ፡ አናቅጽት ፡ ፲፬(ሀ) ፡ እና ፡ ፲፬(ለ) ፡ ደግሞ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ካፒታልን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ ድንጋጌ ፡ አናቅጽት ፡ ፭(፩) ፡ እና ፡ ፭ (፪) ፡ ተተክተዋል ።[12] የድንጋጌው ፡ ደንቦች ፡ በተጨማሪ ፡ ለእርሻና ፡ ለቱሪዝም ፡ ሥራዎች ፡ ይህንን ፡ ነፃነት ፡ ሰጥተዋል ። የገቢው ፡ ግብር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፬ (ለ) ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነው ፡ የዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ አንቀጽ ፡ ፭ (ለ) ፡ በድርጅቱ ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ የተደነገገ ፡ ነው ።

በአንቀጽ ፡ ፭(፪) ፡ መሠረት ፡ ተፈላጊው ፡ መስፋፍያ ፡ ካፒታል ፡ ወደ ፡ ፵ሺ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ ዝቅ ፡ ብሏል ። እንዲሁም ፡ ነፃነት ፡ የሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ዝቅ ፡ ተደርጓል ። ሚኒስትሩ ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችለውን ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ "እስከ ፡" በሚለው ፡ ቃል ፡ አለመኖር ፡ የተነፈገ ፡ ይመስላል ።

በኢትዮጵያ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ደንቦች ፡ በተጨማሪ ፡ ያሻሻለው ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን ፡) በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡[13] ነው።ይህ ፡ አዋጅ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፰ ፡ ቀንና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚጀምሩት ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ። ዋናው ፡ ለውጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የግል ፡ ካፒታል ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የሚያነቃቃና ፡ የሚያበረታታ ፡ አንድ ፡ መደበኛ ፡ ኮሚቴ ፡ መቋቋሙ ፡ ነው ።

የዚህም ፡ ኮሚቴ ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ ገንዘባቸውን ፡ (ካፒታላቸውን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሉ ፡ የሚችሉ ፡ ሆነው ፡ በዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ የቀረጥ ፡ ነፃ ፡ መሆንና ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ሊያገኙ ፡ የሚገባቸውን ፡ እንደዚሁም ፡ ሌላ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥቅምና ፡ መብት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ እያጠና ፡ ሃሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ የ፲፱፻፶፱ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፡ እና ፡ የ፲፱፻፶፯ ፡ ድንጋጌ ፡ ይመሳሰላሉ ። በዚሁ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒ

11 ከዚያው ።

12 የውጪ ፡ አገርና ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ- ም- የወጣ ፡ ድንጋጌ ።

13 በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ - ም- የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ቊጥር ፡ ፪፻፶፪ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፮ኛ ዓመት ፤ ቊጥር ፡ ፪ ፡ (፲፱፻፶፱) ።

14 ከዚያው ።

ስትሩ ፡ ድርጅቶችን ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ በኮሚቴው ፡ አሳሳቢነት ፡ ሳይሆን ፡ በኮሚቴው ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ አንድ ፡ ድርጅት ፡ ሲስፋፋ ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ክፍል ፡ ሲከፈት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ተጨማሪ ፡ ካፒታል ፡ ወደ ፡ ፪፻ሺ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ ዝቅ ፡ ተደርጓል ። ይኸውም ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ሲቋቋም ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ካፒታል ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ።

## ፪/ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ፡ ምሕረት ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ እና ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ሕጎች ።

አሁን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የ፲፱፻፶፱ ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ፡ ስለማዋል ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ እና ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የሌሎች ፡ አገሮችን፡ ሕጎች ፡ ማነጻጸር ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ። አስቀድመን ፡ በነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ዓይነተኛ ፡ ደንቦች ፡ እንመለከታለን ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ እንመለሳለን ።

### ከግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ጊዜና ፡ የነፃነቱ ፡ መጠን ።

ከግብር ፡ ነፃነት ፡ የሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በየአገሩ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። በፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ሕግ ፡ ጊዜውን ፡ በአስራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ወስኖታል ። የ፲፱፻፵፯ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አስር ፡ ዓመት ፡ ዝቅ ፡ አድርጎታል ።[15] በሜክሲኮ ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጊዜው ፡ አስር ፡ ሰባት ፡ ወይም፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ጊዜው ፡ የሚለያየው ፡ እንዱስትሪ፡ "በአንደኛ፡ ደረጃ ፡ ተፈላጊ ፡" "መካከለኛ ፡" ወይም ፡ "በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተፈላጊ ፡" በሚሆን በት ፡ መጠን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ "ልዩ ፡ አስተያየት ፡ የተሰጠው ፡ ኩባንያ ፡" በሚለው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ከሆነ ፡ ከዚህ ፡ በጣም ፡ ሊያጥር ፡ ይችላል ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ደንብ ፡ በሜክሲኮ ፡ እና ፡ በፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ።[16] ይህ ፡ ደንብ ፡ ተመሳሳይ ፡ ዕቃዎችን ፡ የሚሠሩትን ፡ ኩባንያዎች ፡ ሁሉ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ያደርጋቸዋል ። የሚያገለግለው ፡ ግን ፡ በመጀመሪያ ፡ የተሰጠው፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ እስከሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ደንብ ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ የተደረገው ፡ ድርጅት ፡ ይህ ፡ ነፃነት ፡ ካልተሰጣቸው ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ ይኖረው ፡ ነበር ።

የግብሩ ፡ ነፃነት ፡ መጠንም ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ሊለያይ ፡ ይችላል ። ሕጉ ፡ በከፊል፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ኩባንያውን ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። ለምሳሌ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ የሜክሲኮ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የገንዘብና ፡ የብድር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከኤኮኖሚው ፡ ሚኒስትር ፡[17] ጋር ፡ ከተወያየ ፡ በኋላ ፡ የግብሩን ፡ ነፃነት ፡ መጠን ፡ በፈቃዱ ፡ ለመወሰን ፡ ይችል ፡ ነበር ። ከ፲፱፻፶፪ ፡ ጀምሮ ፡ ግን ፡ የግብሩ ፡ ነፃነት ፡ የጠቅላላው፡ ግብር ፡ (መከፈል ፡ የሚገባው ፡) አርባ ፡ መቶኛ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኖአል ።[18] በፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ ደግሞ ፡ በ፲፱፻፵ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ (እ- ኤ- አ-) በወጡት ፡ ሕጎች ፡

---

15 ኮፍማን ፤ ኢንካም ፡ ታክስ ፡ ኤክዘምፕሽን ፡ ኤንድ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ደቬለፕሜንት ፡ (፲፱፻፶፱) ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ፡ (ከአሁን ፡ በኋላ ፡ ኮፍማን ፡ ተብሎ ፡ የሚጠቀስ) ።

16 ከዚያው ።

17 ሎው ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ዲቬለፕሜንት ፡ ኦቭ ፡ ኒው ፡ ኤንድ ፡ ኔሰሰሪ ፡ ኢንዱስትሪስ ፤ ኦፊሻል ፡ ጋዜት ፤ ጃንዋሪ ፡ ፬ ፤ ፲፱፻፶፭ ፤ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ (ከአሁን ፡ በኋላ ፡ የ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ- ም- የሜክሲኮ ፡ ሕግ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠቀስ) ።

18 ኮፍማን ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ።

መሠረት ፡ ከግብር ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ እንዲሰጥ ፡ ተወስኗል ። የግብሩም ፡ ነፃነት ፡ በተጨማሪ ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ በሚከፈሉ ፡ ግብሮችና ፡ ለማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ በሚከፈሉ፡ ግብሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ተደርጓል ።[19]

## ነፃ ፡ ለመሆን ፡ የሚያበቁ ፡ ሁኔታዎች ።

ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሕጐች ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ ለማናቸውም፡ የልማት ፡ ድርጅት ፡ ይህንን ፡ ዕድል ፡ አይሰጡም ። በሄለርና ፡ ኮፍማን ፡ አስተያየት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚከተለው ፡ እና ፡ በብዙዎች ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ የሚነገረው ፡ አንድ ፡ መለኪያ ፡ ይህ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ዕድል ፡ በእርግጥ ፡ ለሚያስፈልጋቸው ፡ ሥራዎችና ፡ የፋብሪካቸው ፡ ውጤት ፡ ደግሞ ፡ ለአገሪቱ ፡ "አዲስ" ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።[20]

ለምሳሌ ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የሜክሲኮ ፡ ሕግ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ መሆንን ፡ የሚፈቅደው ፡ ለ "አዲስ" ወይም ፡ ለ"ተፈላጊ" ፋብሪካዎች ፡ (እንዱስትሪዎች ፡) ብቻ ፡ ነው ።[21] እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ እራሳቸው ፡ "በአንደኛ" ፡ "በመካከለኛ ፡" ወይም ፡ በ"ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡[22] ተፈላጊ ፡" በሚባሉ ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ተሸንሽኗል ። የዚህም ፡ መከፋፈል ፡ ቀዋሚ ፡ ምክንያት ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ዕድል ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ መቆየት ፡ እንዳለበት ፡ ለመወሰን ፡ እንዲረዳ ፡ ነው ። አንድ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በየትኛው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ሥር ፡ እንደሚመጣ ፡ ለማወቅ ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ እንዱስትሪ ፡ ለሜክሲኮ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚጠቅም ፡ መረዳት ፡ ያሻል ። በ፲፱፻፶፭ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጡት ፡ የፑዌርቶሪኮ ፡ ሕጐች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጉት ፡ "አዲስ" ፡ ኢንዱስትሪዎችንና ፡ በተባሉት ፡ ሕጐች ፡ ውስጥ ፡ ዝርዝር ፡ ሊስታቸው ፡ ለወጣ ፡ ማበረታታትን ፡ ለሚፈልጉ፡ እንዱስትሪዎች ፡ ነው ።[23] እንደዚሁም ፡ ጋና ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ አዋጅዋ ፡ ነፃ ፡ ያደረገችው ፡ "ተቀዳሚ ፡ እንዱስትሪዎችን፡" (ፖያኒር ፡ ኢንዳስትሪስ፡) ነው ። እነኚህም ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ "ከዚያ ፡ በፊት ፡ በጋና ፡ ግዛት ፡ የሌሉና ፡ ቢኖሩ ፡ ግን፡ የመበልጸጋቸው ፡ ዕድል ፡ ያማረ ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፡" ናቸው ።[24] በፍልፒን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ደግሞ ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ የመውጣቱ ፡ ዕድል ፡ የተሰጠው ፡ ለ "አዲስ ፡ እና ፡ ተፈላጊ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሲሆን ፡ የተባለው ፡ እንዱስትሪ፡" የሥራው ፡ መሠረት ፡ ንግዳዊ ፡ እንዲሆንና ፡ ለአገሪቱም ፡ ኢኮኖሚ ፡ የሚጠቅምና ፡ "በተጨማሪም ፡ ሥራውን ፡ ለማካሄድ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ወጪ ፡ ውስጥ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ዕቃ ፡ ለማስመጣት፡ የሚያወጣው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከ፷ ፡ በመቶ ፡ (ከሥልሳ ፡ በመቶ ፡) ያነሰ ፡" መሆን ፡ ይኖርበታል ።[25] የነዚህ ፡ አራት ፡ አገሮች ፡ ሕጐች ፡ አንድ ፡ ዓላማ ፡ ያላቸው ፡ ይመስላል ። ይኸውም ፡ ገና ፡ ያልተቋቋሙ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ተቋቁመው ፡ ግን ፡ አገሪቷ፡

19 በዚያው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፳፰ ።

20 ሄለር ፡ ኤንደ ፡ ኮፍማን ፤ ታክስ ፡ ኢንሴንቲቭስ ፡ ፎር ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ኢን ፡ ሌስ ፡ ዲቬለፐድ ፡ ካንትሪስ ፡ (፲፱፻፷፫) ፤ ገጽ ፡ ፵፪ ። (ከአሁን ፡ በኋላ ፡ ሄለር ፡ ኤንደ ፡ ኮፍማን ፡ ተብሎ ፡ የሚጠቀስ) ።

21 ሮዝ ፡ ኤንደ ፡ ክርስተንሰን ፤ ገጽ ፡ ፺፮ ።

22 ከዚያው ።

23 ኮፍማን ፤ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ።

24 ኤ ፡ ኤች ፡ ስሚዝ ፡ ታክስ ፡ ሪሊፍ ፡ ፎር ፡ ኒው ፡ ኢንደስትሪስ ፡ ኢን ፡ ጋና ፤ ፲፮ ፡ ናሽናል፡ታክስ ።

25 ጆርናል ፡ ፫፻፳፪ ፡ (፲፱፻፶፰) ።
ኮፍማን ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ።

በምትፈልገው ፡ መጠን ፡ ተደላድለው ፡ የማይገኙ ፡ እንዱስትሪዎችን ፡ ማዳበርና ፡ ማበረታታት ፡ ነው ።

ሌላው ፡ ተመሳሳይነታቸው ፡ ደግሞ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የማድረጉን ፡ ዕድል ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ ድርጅቶች ፡ ብቻ ፡ መወሰናቸው ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፖርቶ ፡ ሪኮን ፡ አዋጅ ፡ ፍላጐት ፡ ለሚሟላት ፡ አንድ ፡ (የሥራ) ፡ ድርጅት ፡ አንድ ፡ "የተጣራ ፡ ውጤት" ፡ ሠርቶ ፡ ማውጣት ፡ ነበረበት ። "የተጣራ ፡ ውጤትም ፡" ከጥሬ ፡ ሸቀጣሸቀጦች ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ዕቃ ፡ በሰው ፡ እጅም ፡ ሆነ ፡ በማጣሪያ ፡ መኪና ፡ በተለወጡት ፡ ውጤቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ በአስፈጻሚው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ የውጤቱ ፡ ዋጋ ፡ በአሠራሩ ፡ በአቀራረቡም ፡ ሆነ ፡ በጥራቱ ፡ በሚገባ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።[26]

የ፲፱፻፶፫ቱ ፡ የሜክሲኮ ፡ ሕግ ፡ እንደሚለው ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ድርጅት ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ከበፊቱ ፡ ውጤቱ ፡ ፲በመቶ ፡ (አሥር ፡ በመቶ) ተጨማሪ ፡ ማውጣት ፡ ያስፈልገዋል ።[27] ይህ ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ "ድርጅቱ ፡ ለአገሪቱ ፡ ኢኮኖሚ ፡ በደንብ ፡ የሚረዳ ፡ መሆኑን"[27] ለማረጋገጥ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የእንዱስትሪው ፡ ድርጅት ፡ ለሚያወጣው ፡ ነገር ፡ የሚያደርገው ፡ ወጭ ፡ ፳ ፡ በመቶ ፡ (ሥልሳ ፡ በመቶ) ፡ በሜክሲኮ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልግ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ግዴታ ፡ "ከውጭ ፡ አገሮች ፡ በሚገዙ ፡ ጥሬ ፡ ሸቀጣሸቀጦች ፡ (ሮው ፡ ማቴሪያልስ) ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ ወጭ ፡ እንዲቀነስ" ፡[29] ያደርገዋል ።

ይህንን ፡ የመሰሉ ፡ ሕጐች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ መሆንን ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ ድርጅቶች ፡ ብቻ ፡ በመወሰን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ድርጅቱ ፡ ከበፊቱ ፡ ውጤቱ ፡ በላይ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ መጠን ፡ እንዲያክል ፡ በመጠየቅ ፡ በሙሉ ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ በከፊል ፡ አገሪቱ ፡ ልትከተለው ፡ የሚገባውን ፡ የእድገት ፡ ጐዳና ፡ ያመለክታሉ ። እነዚህ ፡ ሕጐች ፡ ተፈጻሚ ፡ በመሆናቸው ፡ መጠን ፡ ገንዘብን ፡ በንግድ ፡ በእርሻና ፡ በሌሎች ፡ ዋና ፡ አገር ፡ በሚያፈራቸው ፡ ነገሮች ፡ (ፕሮዳክት ፡ ለምሳሌ ፡ ቡና ፡ እጥበት)፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋል ፡ ወደ ፡ እንዱስትሪ ፡ ልማት ፡ እንዲዞሩ ፡ ያደርጋሉ።

## የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ።

የኢትዮጵያው ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ እላይ ፡ ከመረመርናቸው ፡ በብዙ ፡ መንገዶች ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ነው ። በጠቅላላ፡ አነጋገር ፡ እነኚህን ፡ ልዩነቶች ፡ የፈጠሩት ፡ የአዋጁ ፡ በአጠቃላይ ፡ ቋንቋ ፡ መጠቀምና ፡ አሳሳቢና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያጋጥሙ ፡ ለሆኑ ፡ ችግሮች ፡ ሥፍራ ፡ አለመስጠቱ፡ ነው ።

አዋጁ ፡ "ልዩ ፡ አስተያየት ፡ የተሰጠው ፡ ኩባንያ ፡" ስለሚባለው ፡ ጉዳይ ፡ አይናገርም ። በአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ መሠረት ፡ ሊደረግ ፡ የሚቻለው ፡ አንዱ ፡ ነገር ፡ የልማቱ ፡ ድርጅት ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ አለመሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። አዲስ ፡ የተቋቋመው ፡ የልማት ፡ ድርጅት ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ ተቋ

---

26 ቴይለር ፡ ገጽ ፡ ፺፩ ።

27 ሮዝ ፡ ኤንድ ፡ ክርስተንሰን ፤ ገጽ ፡ ፳፱ ።

28 ከዚያው ።

29 በዚያው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፭ ።

ቁሞ ፡ ከነበረው ፡ ድርጅት ፡ ይበልጥ ፡ ጥቅም ፡ እንደሚያገኝ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ካፒታልን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ የተቋቋመው ፡ ኮሚቴ ፡ ለተባለው ፡ አዲስ ፡ ድርጅት ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑን ፡ መብት ፡ ከመፍቀድና ፡ ወይም ፡ ካለመፍቀድ ፡ መምረጥ ፡ ይኖርበታል ። በፊት ፡ ተቋቁመው ፡ ያሉት ፡ ድርጅቶች ፡ "ልዩ ፡ አስተያየት ፡ የተሰጠው ፡ ኩባንያ ፡" በሚለው ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚሆኑ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ችግር ፡ ባልተፈጠረ ፡ ነበር ።[30]

ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ በሚያበቁት ፡ ፫ ፡ ሁኔታዎች ፡ በኩልም ፡ አዋጁ፡ ጥብቅ ፡ እንዳልሆነ ፡ ይታያል ። በብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ "ከገቢ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆን ፡ ዕድል ፡ የሚሰጠው ፡ ሥራቸውን ፡ በኩባንያ ፡ መስክ ፡ የሚያካሄዱና ፡ ብዙውንም ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የተመሠረቱ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።"[31] በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ በፖርቶ ፡ ሪኮ ፡[32] እና ፡ በእሥራኤል ፡ እንደሚደረገው ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ዕድል ፡ የድርጅቱ ፡ ሕጋዊ ፡ አመሠራረት ፡ ወይም ፡ ዜግነት ፡ ሳይመረመር ፡ ለማናቸውም ፡ (ድርጅት) ፡[33] የተሰጠ ፡ ይመስላል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ከሌሎቹ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ የሚለይበት ፡ ሌላው ፡ ሁኔታ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልጉት ፡ ድርጅቶች ፡ "አዲስ ፡" "ተፈላጊ ፡" ወይም ፡ "ተቀዳሚ ፡" እንዲሆኑ ፡ አለማስፈለጉ ፡ ነው ። ይህም ፡ በመሆኑ ፡ ለመቋቋም ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ የማያስፈልጋቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ነፃ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ መንግሥት ፡ ለሌላ ፡ የእድገት ፡ ሥራ ፡ ሊያውለው ፡ የሚችለው ፡ ገቢ ፡ ተቀነሰበት ፡ ማለት ፡ ነው ። ከግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ መብት ፡ ለድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ አገሪቷ ፡ ከብዙዎች ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ በልማት ፡ ያነሰች ፡ ስለሆነች ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ድርጅቶች ፡ እንደ ፡ "አዲስ ፡" "ተፈላጊ ፡" ወይም ፡ "ተቀዳሚ ፡" ሊቆጠሩ ፡ ይችላል ፡ በሚል ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ይሆናል ። በተጨማሪም ፡ በአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ መሠረት ፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ የሚፈቅደው ፡ "ካፒታልን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ በተቋቋመው ፡ ኮሚቴ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡"[34] የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ የሚገባቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በኮሚቴው ፡ አስተያየት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የኤኮኖሚ ፡ እድገት ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ብቻ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያደርግ ፡ ይሆናል ።

ኮሚቴው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ካለው ፡ ውሳኔዎቹ ፡ ለአዋጁ ፡ አፈጻጸም ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ አመልካቾች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ለመሆን፡ ያቀረቡትን ፡ ጥያቄ ፡ ለመፍቀድ ፡ ወይም ፡ ላለመፍቀድ ፡ ለኮሚቴው ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ በሚገባ ፡ ስላልተገለጸ ፡ ይህ ፡ በአመልካች ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ ጥርጣሬን ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ካፒታ

30 አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለችበት ፡ የእድገት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ፕሮብሌም ፡ በጣም ፡ አሳሳቢ ፡ አይሆንም ። ምክንያቱም ፡ ውድድር ፡ ሊያጠቃቸው ፡ የሚችል ፡ ድርጅቶች ፡ ቊጥር ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ስለሆነ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፤ የአገሪቷ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ እየተፋጠነ ፡ ሲሄድ ፡ ይህ ፡ ፕሮብሌም ፡ አሳሳቢ ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም ።

31 ሄለር ፡ ኤንደ ፡ ኮፍማን ፤ ገጽ ፡ ፳፬ ።

32 በዚያው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፴፬ ፡ ላይ ፤ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፳፰ ።

33 የተተወው ፡ ታላቁ ፡ ክፍል ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶችን ፡ የሚጠቀልለው ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

34 በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ - ም - የወጣ ፡ አዋጅ ፤ አንቀጽ ፡ ፳ ።

ልን ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ለሚያውሉ ፡ ሰዎች ፡ ብዙም ፡ ነገር ፡ አይነግራቸውም ። እንግዲህ ፡ አንድ ፡ አመልካች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑን ፡ ዕድል ፡ ለመገመት ፡ ሕጉ፡ እንዲፈጸሙ ፡ የመደባቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ለመፈጸም ፡ ኰሚቴው ፡ የሚጠቀምባቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ደንቦች ፡ ማወቅና ፡ በተጨማሪም ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሌላ ፡ (ለምሳሌ ፤ ድርጅቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ኤኰኖሚ ፡ ዕድገት ፡ ያለው ፡ ጥቅም ፡) ነገሮችን ፡ አጣምሮ ፡ ይመለከት ፡ እንደሆነ ፡ ማወቅ ፡ ይኖርበታል ።[35] ኰሚቴው ፡ የሚጠቀምባቸውን ፡ ደንቦች ፡ በአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን፡ መሠረት ፡ ሊያወጣ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኰሚቴው ፡ ደንብ ፡ ለማውጣት ፡ የዘገየ ፡ መሆኑንና ፡ እስከአሁንም ፡ የሚጠቀምባቸው ፡ የታወቁ ፡ ደንቦች ፡ እንደሌሉ ፡ ፀሐፊው ፡ ገምቷል ። ኰሚቴው ፡ ውሳኔዎቹን ፡ ባልተዛነፈ ፡ ሁኔታ ፡ ለማካሄድና ፡ የኢትዮጵያንም ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ ለማፋጠን ፡ ለውሳኔዎቹ ፡ መሠረት ፡ የሚሆኑትን ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦችን ፡ መደንገግና ፡ ለሕዝብ ፡ ማስታወቅ ፡ ይኖርበታል ።

ኰሚቴው ፡ ሊያብራራቸው ፡ ከሚገባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ከሚችሉት ፡ ድርጅቶች ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ "የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ" ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ መግለጽ ፡ ነው ። አንድ ፡ ድርጅት ፡ በፊት ፡ ከሚያፈራው ፡ ፍሬ ፡ በላይ ፡ ትንሽ ፡ ያስበለጠ ፡ እንደሆነ ፤ ለምሳሌ ፡ ሬዲዮ ፡ ወይም ፡ አውቶቡሶችን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በመጡ ፡ ዕቃዎች ፡ ቢያገጣጥም ፡ ወይም ፡ የቡና ፡ ማጣሪያ ፡ ቢተክል፡ "ኢንዱስትሪ ፡" ይባላልን? ኰሚቴው ፡ በአንቀጽ ፡ ፫(፪) ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንደ፡ "ኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡" እንዲቆጠር ፡ የሆነው ፡ መሣሪያ ፡ ዋጋ ፡ ወጪ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ክፍል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መገኘት ፡ አለበት ፡ ወይ ? እነኝህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚሆኑትን ፡ ድርጅቶች ፡ በሚዘረዝሩት ፡ የፓቶሪኮና፡ የሜክሲኰ ፡ ሕጐች ፡ ውስጥ ፡ በመጡት ፡ መልስ ፡ አግኝተዋል ።

## ፫/ <u>ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነትን ፡ መስጠት ፡ ካፒታልን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለመሳብ ፡ ያለው ፡ ጥቅም ።</u>

የአብዛኞዎቹ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነትን ፡ የሚሰጡት ፡ ሕጐች ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ካፒታልን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋልን ፡ ችግር ፡ በማቃለል ፡ የኤኰኖሚ ፡ እድገት ፡ ለማፋጠን ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ እንደተደረገው ፡ ሕጉ ፡ የአገር ፡ ውስጥና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባለካፒታሎችን ፡ እንዲያጠቃልል ፡ ተደርጐ ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ።[36] ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ለኤኰኖሚ ፡ እድገት ፡ የሚበቃ ፡ የአገር፡ ውስጥ ፡ ካፒታል ፡ ስለሌላቸው ፡ ሕጐቹ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚመለከቱት ፡ ገንዘባቸውን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባለካፒታሎችን ፡ ነው።

እንግዲህ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሕጐችን ፡ ጥቅም ፡ ስንመረምር ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ አገሪቱ ፡ የማይመጣውን ፡ ካፒታል ፡ ሕጉ ፡ በመኖሩ፡ ወደ ፡ አገሪቱ ፡ በመሳብ ፡ ላይ ፡ ነውን? የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ መጠየቅ ፡ ያስፈልጋል ። ግን ፡ በሕጉ ፡ የሚጠቀሙ ፡ ድርጅቶችን ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርገው ፡ ሕግ፡ ቢኖርም ፡ ባይኖርም ፡ መቋቋማቸው ፡ የማይቀር ፡ ከሆነ ፡ መንግሥት ፡ የቀረጥ ፡ ገቢውን ፡ አጣ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አላተረፈም ፡ ማለት ፡ ነው ። ብዙ ፡ አገሮች ፡ የራሳ

---

35 ቀደም ፡ ብለው ፡ ማመልከቻ ፡ ያቀረቡት ፡ ሰዎች ፡ ያገኙትን ፡ ጥቅም ፡ መመልከትም ፡ ወደፊት ፡ ገንዘቡን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው ፡ ያለውን ፡ ዕድል ፡ ለመገመት ፡ ይረዳል ።

36 ለምሳሌ ፡ ያህል ፤ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ - ም- የሜክሲኮ ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ይመለከቷል ፡- "የዚህ ፡ ሕግ ፡ ዓላማ ፤ አዳዲስ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ድርጅቶች ፡ እንዲቋቋሙና ፡ ያሉትም ፡ እንዲሻሻሉ ፡ የሚያበረታታ ፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ በመስጠት ፤ የብሔራዊ ፡ ኢንዱስትሪን ፡ ዕድገት ፡ ማፋጠን ፡ ነው ።"

ቸውን ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የማድረግ ፡ ፖሊሲ ፡ ሲደግፉ ፣ ይህ ፡ ፖሊሲ ፡ ለፓርቶ ፡ ሪኮ ፡ እንዴት ፡ እንደጠቀማት ፡ ይጠቅሳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ቴይለር ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ ከሌሎች ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ በተለየ ፡ ሁኔታ ፡ እንደምትገኝና ፡ እንደርሷ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ማውጣትን ፡ ከመደገፍ ፡ አስቀድሞ ፦ ፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ በዋናው፡

> የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ታሪፍ ፡ ክፍል ፡ ስትገኝ ፣ ከፌድራል ፡ ታክስ ፡ ነፃ ፡ የመሆን ፡ ዕድል ፡ እንዳላት ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ።[37]
>
> በተጨማሪም ፡ ፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነት ፡ ከሰጡት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ፡ ልዩ ፡ ነች ። የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ባለሀብቶች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ሲያውሉ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ የታክስ ፡ ነፃነት ፡ የሚያገኙባት ፡ አገር ፡ ነች ።[38]

ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የማድረጉ ፡ ሕግ ፡ ፑዌርቶ ፡ ሪኮን ፡ በጠቀማት ፡ ልክ ፡ ሌሎችንም ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ይጠቅማቸዋልን? የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ሲቀርብ ፣ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፑዌርቶ ፡ ሪኮና ፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ግንኙነት፡ በሚገባ ፡ ሳይመረመር ፡ ይታለፋል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ቴይለር ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ጀመሩት ፡ ኩባንያዎች ፡ ያደረገው ፡ ጥናት ፡ እንደሚያስረዳው ፣ በእርግጥ ፡ የፑዌርቶ፡ ሪኮ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የማድረግ ፡ ሕግ ፡ ለአገሪቷ ፡ ዕድገት ፡ ረድቷል ። ከተጠየቁት ፡ ፵፫ ፡ ኩባንያዎች ፡ ፴፩ዱ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ፑዌርቶ ፡ ሪኮን ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ለመጀመር ፡ ተፈላጊ ፡ እንዳደረጋት ፡ ገልጸዋል ።[39] “ይህ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርገው ፡ ሕግ ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ (በፑዌርቶ ፡ ሪኮ) ፡ ትጀምሩ ፡ ነበርን ?” ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ሲመልሱ ፣ ከ፵፬ቱ ፡ ፴፯ቱ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ (፹፬ ፡ በመቶ) ፡ “ይህ ፡ ሕግ ፡ ባይኖር ፡ ኖሮ ፡ (ሥራውን) ፡ አለመጀመራቸውን” ፡ ገልጸዋል ።[40] ነገር፡ ግን ፡ ቴይለር ፡ ይህን ፡ መልስ ፡ “ጊዜው ፡ ካለፈ ፣ ማለት ፣ ኢንዱስትሪዎቹ ፡ ከተቋቋሙ ፡ በኋላ ፡ ስለተሰጠ ፡” እምብዛም ፡ አልተቀበለውም ።[41] ለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሲሰጥ ፡ የተቋቋሙት ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆን ፡ መብታቸው ፡ እንዳይቀር ፡ ጠቃሚነቱን ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ያጋንናሉ ፡ ብሏል ።

ሮስና ፡ ክርስቲያንሰን ፡ በሜክሲኮ ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ጥናት ፡ አድርገው ፡ ነበር። እነሱ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ስለሚያደርግ ፡ ሕግ ፡ መኖር ፡ ጥቅም ፡ (ሳቢነት) ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ሊታሰብበት ፡ የሚገባ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ከፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ ይልቅ ፡ የሜክሲኮ ፡ ሁኔታ ፡ ከሌሎቹ ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ስለሚመሳሰል ፡ ነው ። ሮስና ፡ ክርስቲያንሰን ፡ “ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ መብት ፡ ካፒታልን ፡ በሜክሲኮ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ብቻውን ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ የሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ አይመስልም ፤ እንዲያውም ፡ ከዋናዎቹ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ የሆነበት ፡ጊዜ ፡ ያለም ፡ አይመስልም ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሜክሲኮ ፡ ውስጥ ፡ ካፒታልን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሲታሰብ ፣ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርግ ፡ ሕግ ፡ መኖሩ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ አልታሰበበትም ፡” ፡[42] ሲሉ ፡ ጽፈዋል ።

---

37 ቴይለር ፤ ገጽ ፡ ፳ ።
38 ከዚያው ።
39 ቴይለር ፤ ገጽ ፡ ፩፻፳፬ ።
40 በዚያው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፩፻፳፱ ።
41 ከዚያው ።
42 ሮዝ ፡ ኤንድ ፡ ክርስተንሰን ፤ ገጽ ፡ ፩፻፩ ።

እንግዲህ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የማድረግ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ሕጉ ፡ ባይወጣ፡ ኖሮ ፡ የማይመጣውን ፡ የውጭ ፡ ካፒታል ፡ ለመሳብ ፡ ከሆነ ፡ በሜክሲኮ ፡ በተደረገው ጥናት ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ እንደማይረዳ ፡ ያሳያል ፤ እንደዚህም ፡ ከሆነ ፡ ደግሞ ፡ በሌላውም ፡ ቦታ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነው ።[43] ሌሎችም ፡ ታዛቢዎች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርግ ፡ ሕግ ፡ ጥቅም ፡ አጠራጣሪ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ።[44]

ከገቢ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርገውን፡ ሕግ፡ ጥቅም፡ አጠራጣሪ ፡ የሚያደርገው፡ አንዱ፡ ምክንያት ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ጉዳይ ፡ ካፒታሉን ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚፈልገው፡ ባለሀብት ፡ ውሳኔውን ፡ ከሚመሰርትባቸው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው ። በሄለርና ፡ ካፍማን ፡ አስተያየት ፤

የግብር ፡ ነፃነት ፡ ከሌሎች ፡ እድገትን ፡ ከሚያበረታቱ ፡ ምክንያቶች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ ጥቅሙ ፡ አነስተኛ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ይቻላል ።
በተጨማሪም ፤

ይህ ፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ ከብዙዎቹ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነና ፡ በተለይም ፡ በኤኮኖሚ ፡ ታዳጊ ፡ በሆኑ ፡ አገሮች ፡ ያለው ፡ ጥቅም ፡ አነስተኛ ፡ ስለሆነ ፤ በአገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ካፒታል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ለዚህ ፡ ምክንያት ፡ የማይገባ ፡ ግምት ፡ መስጠት ፡ ይሆናል ።[45]

ከገቢ ፡ ላይ ፡ የሚከፈለው ፡ ግብር ፡ መጠን ፡ አነስተኛ ፡ በሆነበት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ አስተያየቶች ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ ይኖራቸዋል ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ የሚከፈለው ፡ መደበኛ ፡ ግብር ፡ በመቶ ፡ ሐያ[46] ፡ (፳ ፡ በመቶ) ፡ ነው ። ግብር ፡ የሚከፈልበት፡ ገቢ ፡ ከሠላሳ ፡ ሺ ፡ የኢትዮጵያ፡ ብር ፡ (፴ሺ)[47] ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ በመቶ ፡ አሥር ፡ (፲በመቶ) ፡ ሰር ፡ ታክስ ፡ (ተጨማሪ ፡ ታክስ) ፡ ይከፈልበታል ፤ ከመቶ ፡ አምሳ ፡ ሺ ፡[48] (፩፻፶ሺ)፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ አሥር ፡ በመቶ ፡ (፲በመቶ) ሰር ፡ ታክስ ፡ ይከፈልበታል። ይህ ፡ የግብር ፡ አከፋፈል ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ (፭ሚሊዮን)፡ ወይም ፡ የበለጠ ፡ ካፒታል ፡ ያወጡና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ሲገኙ ፡ ከፍ ፡ ይላል ። በማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ የሚከፈለው ፡ ግብር ፡ ከ፳፭ ፡ በመቶ ፡[49] (፳፭ ፡ በመቶ) ፡ የሚበል

43 ኮፍማን ፡ በተጨማሪ ፤ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርጉት ፡ የፒዮርቶ ፡ ሪኮ ፡ ድንጋጌዎች ፡ "ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የፈለጉትን ፡ ሰዎች ፡ በማበረታታት ፡ በኩል ፡ ረድተዋል" ፡ የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛነት ፡ ይጠራጠራል ። ኮፍማን ፤ ገጽ ፡ ፴፯ ።

44 ሄለር ፡ ኤንድ ፡ ኮፍማንን ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ይመለከቷል ።

45 ሄለር ፡ ኤንድ ፡ ኮፍማን ፤ ገጽ ፡ ፳ ።

46 ማናቸውንም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፸፫ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳ኛ ፡ ዓመት ፤ ቍጥር ፡ ፲፫ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ (ለ) ፡ (፩) ፡ (፲፱፻፶፫) ፤ የ፲፱፻፷ ፡ ዓ· ም· አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፶፭ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ እንዳሻሻለው ።

47 አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፸፫ ፤ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፳፩ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፫ (ሀ) ።

48 አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፸፫ ፤ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፳፪ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፫ (ለ) ።

49 አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፸፫ ፤ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፳፪ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፬ ።

ጠው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ የግብር መጠኖች ፡[50] ሲተያይ ፡ በጣም ፡ መጠነኛ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ቴይለር ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ አንዳንድ ፡ ስቴቶችና ፡ አውራጃ ዎች ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ቦታቸውን ፡ እንዲቀያይሩ ፡ ለማበረታታት ፡ ያደረጉት ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነት ፡ ውጤት ፡ ሳያስገኝ ፡ ቀርቷል ፤ ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ ብቻውን ፡ በኢንዱ ስትሪዎች ፡ ላይ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ "የሠራተኞች ፡ አበል ፡ የቦታው ፡ ከገበያ፡ ጥሬ ፡ ሸቀጣሸቀጦች ፡ (ሮው ፡ ማቴሪያልስ) ፡ ከሚገኙበት ፡ ቦታ ፡ መራቅ ፡"[51] የመሳ ሰሉትን ፡ ችግሮች ፡ ሊያስወግድ ፡ ስለማይችል ፡ ነው ፡" ይላል ። ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ዕድል ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ለንብረት ፡ ሲሆን ፡ ከዚህም ፡ ግብር፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ ብዙ ፡ ወጭ ፡ አይቀንስም ። ኢትዮጵያም ፡ የወሰደችው ፡ እርምጃ ፡ ይኸ ንኑ ፡ የሚመስል ፡ ነው ። በዝቅተኛ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረግ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ በሌላ ፡ ወጭ ፡ ምክንያት ፡ በአገሪቷ ፡ ውስጥ ፡ ካፒታሉን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ያልቆረጠውን ፡ ባለንብረት ፡ ለመሳብ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ያስቸግራል ።

ምናልባትም ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሕግ ፡ እንድንደግፍ ፡ የሚ ያደርገውን ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ "ይህ ፡ (ሕግ) ፡ ያንድን ፡ ቦታ ፡ ምቹነት ፡ እንደማስታ ወቂያ ፡ ሆኖ ፡ በመግለጽ ፡ አንዳንድ ፡ ባለካፒታሎች ፡ በዚሁ ፡ ብቻ ፡ ተደልለው ፡ ገን ዘባቸውን ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ እንዲያውሉ ፡ ያደርጋቸዋል ፡"[52] የሚል ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚደረገው ፡ ወጭ ፡ ከርሱ ፡ ከሚገኘው ፡ ጥቅም ፡ ይበልጥ ፡ ይሆናል ።

ኪሣራ ፡ የማያስከትል ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ የግብር ፡ ፖሊሲ ፡ ሳይሳካ ፡ ቢቀርም ፡ ጉዳት ፡ የለውም ፤ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነትን ፡ መስጠት ፡ ግን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኪሣራ ፡ ሊያ ስከትል ፡ ይችላል ። ብዙዎች ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ የገቢ ፡ ምንጫቸው ፡ በጣም ፡ የተወ ሰነ ፡ ነው ፤ የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ኢንዱስትሪዎችን ፡ ከግብር ፡ ነፃ፡ ማድረጉ ፡ የመንግሥትን ፡ ገቢ ፡ በይበልጥ ፡ ይቀንሰዋል ። ለኢንዱስትሪዎች ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነትን ፡ መስጠት ፡ "በመሠረታዊ ፡ ልማትና ፡ ለዚህ ፡ ልማት ፡ በየዓመቱ ፡ ለሚደረገው ፡ ወጭ ፡ ምንጭ ፡ በሆነው ፡ በአንዱ ፡ በሚያስተማምን ፡ ምንጭ ፡ መካ ከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ያስፋፋዋል ።"[53] ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረጉ ፡ የሚያደር ሰው ፡ ኪሣራ ፡ ከታወቀ ፡ ይህን ፡ ማስረዳቱ ፡ የፖሊሲው ፡ ደጋፊዎች ፡ ኃላፊነት ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ነው ። ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረጉ ፡ በእርግጥ ፡ ካፒታልን ፡ መሳ

---

50 ማዕከላዊ ፡ የግብር ፡ ክፍያ ፡ ልክ ፡ የሚባለው፡የግብር ፡ ከፋዩ ፡ በጠቅላላ ፡ የሚከፍለው ፡ ግብር ፡ ለጠቅላላ፡ ገቢው ፡ ተከፍሎ ፡ የሚገኘው ፡ ውጤት ፡ ነው ። ማርጂናል ፡ ( ) ፡ የታክስ ፡ ክፍያ ፡ ልክ ፡ የሚባ ለው ፡ ግን ፡ ግብር ፡ ከፋዩ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ተጨማሪ ፡ ብር ፡ላይ ፡ ታክስ ፡ የሚከፈልበት ፡ ልክ ፡ ነው ። ሁለቱንም ፡ በመቶ ፡ ፲ ፡ የሆኑ ፡ ታክሶች ፡ (ተጨማሪ ፡ ታክሶች) ፡ በሠንጠረዥ ፡ (ሐ) ፡ መሠረት ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ግብር ፡ ከፋይ ፡ ማርጅናል ፡ ( ) ፡ ታክስን ፡ በመቶ ፡ ፴ ፡ ሂሣብ ፡ ይከፍላ ል ፡— ይህም ፡ መንግሥቱ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ብር ፡ ተጨማሪ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ፴ ፡ ሳንቲም ፡ ይወስዳል ፡ ማለ ት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ማዕከላዊው ፡ የግብር ፡ ክፍያ ፡ ልክ ፡ ያነሰ ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ በመቶ ፡ ፵ ፡ የሆነው ፡ የክፍያ ፡ ልክ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ በገቢው ፡ የሚፍ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፤ ቀሪው ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ የሚከፈል በት ፡ በመቶ ፡ ፳ ፡ ወይም ፡ ፴ ፡ ሂሣብ ፡ ነው ።

51 ቴይለር ፤ ገጽ ፡ ፳ ።

52 ኮፍማን ፤ ገጽ ፡ ፳፬ ።

53 ኤ ፡ ኤች ፡ ሰሚዝ ፡ እላይ ፡ ግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፤ ገጽ ፡ ፫፻፳፯ ።

ቡ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ ይህን ፡ ብዙ ፡ ወጭ ፡ የሚያስከትል ፡ ፖሊሲ ፡ መተው ፡ መልካም፡ ይሆናል ።[54]

## ፱· ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ በማድረግ ፡ ፋንታ ፡ ሊተኩ ፡ የሚችሉ ፡ ዘዴዎች ፤

አዲስ ፡ ካፒታልን ፡ ለመሳብ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረግ ፡ ጥሩ ፡ እርምጃ ፡ ካልሆነ ፡ በሱ ፡ ፋንታ ፡ የሚተኩ ፡ ምን ፡ ሌሎች ፡ መንገዶች ፡ አሉ ? አንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በቀጥታ ፡ ማሚያ ፡ (ሳብሲዲ) ፡ መስጠት ፡ እንደ ፡ ዘዴ ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል ፡ ይናገራሉ ።[55] መንግሥት ፡ ይህን ፡ በሚያህል ፡ ካፒታል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ትርፍ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ቢያደርግ ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ቅጣት ፡ ማሚያ ፡ (ሰብሲዲ) ፡ መስጠት ፡ ይቆጠራል ።[56] ለምሳሌ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠው ፡ ማሚያ ፡ ስድስት ፡ በመቶ ፡ (፮ ፡ በመቶ) ፡ ሲሆን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ካፒታል ፡ (፪፻ሺ) ፡ በሥራ፡ ላይ ፡ ያዋለ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ (፲፪ሺ) ፡ ያገኛል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሥራው ፡ በዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚያገኘው ፡ ትርፍ ፡ ከዚህ ፡ አንሶ ፡ ሲገኝ ፡ ልዩነቱን፡ ማሚላት ፡ የመንግሥት ፡ ሃላፊነት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀሙ ፡ አዲስ ፡ ለሆኑ ፡ እንዱስትሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ።[57]

ኩባንያው ፡ ከመንግሥት ፡ የሚያገኘው ፡ ማሚያ ፡ ባተረፈው ፡ ልክ ፡ ሳይሆን ፡ የተወሰነ ፡ ማሚያ ፡ (ሰብስዲ) ፡ ስለሆነና ፡ የገቢ ፡ ግብርም ፡ ስለሚከፈል ፡ መንግሥት፡ ገቢውን ፡ አያጣም ። ነገር ፡ ግን ፡ የአንዱ ፡ ኩባንያ ፡ ኪሣራ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ፡ ቢገኝ ፡ መንግሥት ፡ መካስ ፡ አለበት ። ሥራውንም ፡ በኪሣራ ፡ ምክንያት ፡ የሚያቋርጥ ፡ ኩባንያ ፡ የመንግሥት ፡ ማሚያ ፡ እስኪያገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሥራውን ፡ እየከሰረ ፡ ይቀጥል ፡ ይሆናል ። ግን ፡ ለኩባንያው ፡ ከኪሣራው ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ማሚያ ፡ (ሰብስዲ) ፡ በማድረግ ፡ ይህንን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ከዋለው ፡ ገንዘብ ፡ በየዓመቱ ፡ ፳ ፡ በመቶ ፡ (ሃያ ፡ በመቶ) ፡ ብቻ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ለሦስት ፡ ተከታታይ ፡ ዓመታት ፡ ብቻ ማሚያ ፡ መስጠት ፡ ይቻላል ። ቴይለር ፡ ይኸንኑ ፡ የሚመስል ፡ አስተያየት ፡ ሲሰጥ ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ "ትርፍ ፡ ያላቸው ፡ ኢንዱስትሪዎችን ፡ ሃምሳ ፡ በመቶ ፡ (፶በ፻) ፡ ኪሣራ ፡ መንግሥት ፡ እንዲችላቸው ፡ የሚያደርግ ፡ ሕግ ፡ ቢኖር ፡ መልካም ፡ ነው ። ይህ ፡ ቢደረግ ፡ ኖሮ ፡ አሁን ፡ ለፑዌርቶ ፡ ሪኮ ፡ የገቢ ፡ ታክስ ፡ የሚደረገው ፡ ማሚያ ፡ (ሰብሰዲ)፡

---

54 ቴይለር ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣል ፡- "የገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነትን ፡ በመስጠት ፡ የሚመጣው፡ ጠቅላላ ፡ ኪሣራ ፡ ከፍተኛ ፡ ነው ። ጉዳቱ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ የሚደርስ ፡ እና፡ መልኩን ፡ የለወጠ ፡ የሰሻል ፡ ኪሣራን ፡ የሚያስከትል ፡ ይሆናል የ ---የግብር ፡ ነፃነት ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡— (፩) የግብር ፡ ነፃነት ፡ የሚያስከትለው ፡ የአገር ፡ ገቢ ፡ መቀነስ ፡ ከፍተኛ ፡ ሲሆን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የተደበቀና ፡ ለመገመት ፡ የሚያስቸግር ፡ ነው ። (፪) ፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ አሰጣጫ ፡ የምርጫ ፡ ዘዴ ፡ በጣም ፡ ይጉድለዋል ። (፫) የግብር ፡ ነፃነት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ የመቆየት ፡ ጣቢያ ፡ አለው ። እንዲሁም ፡ ግብር ፡ ሊከፈልባቸው ፡ የሚገባቸውን ፡ አንዳንድ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ክፍሎች ፡ እና ፡ ሌሎች ፡ የፖለቲካ ፡ ክፍሎችን ፡ ወደ ፡ ማጠቃለሉ ፡ ያዘነብላል ። (፬) ፡ የግብር፡ ነፃነት ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ ሁኔታን ፡ ያስከትላል ። (፭) ፡ የግብር ፡ ነፃነት ፡ የግብር ፡ ሸክምን ፡ በሚገባ ፡ ሁኔታ ፡ ለማከፋፈል ፡ የሚደረገውን ፡ ጥረት ፡ ያደክማል ።" ቴይለር ፤ ገጽ ፡ ፩፻፶፪ ።

55 የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፴፪ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰ ።

56 ከመንግሥት ፡ የሚሰጠውን ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ የልማት ፡ ሥራዎችን ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ የሚያስመስሉትን ፡ ሰዎች ፡ ለመቆጣጠር ፡ ተገቢው ፡ እርምጃ ፡ መወሰድ ፡ አለበት ።

57 የገቢው ፡ ግብር ፡ የሚከፈለው ፡ በትርፎች ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ከገቢው ፡ ግብር ፡ ነፃነት ፡ ጥቅም ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለው ፡ የግብሩ ፡ ነፃነት ፡ የተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኝ ፡ ሥራን ፡ የሚያከናውን ፡ ድርጅት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሃምሳ ፡ በመቶ ፡ (፶በ፻) ፡ በተቀነሰ ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ ለማናቸውም ፡ አዲስ ፡ ኩባንያዎች ፡ በመጣሪያ ፡ ላይ ፡ ከሚያውሉት ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ (፲፫በ፻) ፡ እንደሚመለስላቸው ፡ ቢደረግ ፡ የሚደርሰው ፡ የመንግሥት ፡ ወጭ ፡ አሁን ፡ ከሚያደርገው ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ማሚያ ፡ (ሱብሲዲ) ፡ ያንስ ፡ ነበር ።"[58] ለማንኛውም ፡ ብዙዎች ፡ ድርጅቶች ፡ ከተቋቋሙበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ትርፍ ፡ እናገኛለን ፡ ብለው ፡ ስለማያስቡ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረጉ ፡ እምብዛም ፡ አይሰማቸውም ። እንዲህ ፡ የሚያስቡትን ፡ ድርጅቶች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ካዋሉት ፡ ካፒታል ፡ የተወሰነ ፡ መጠን ፡ እንደሚመለስላቸው ፡ ማረጋገጫ ፡ መስጠቱ ፡ ያስደስታቸዋል ።

ሌላው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ዕድል ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ "ነፃ ፡ የመሆኑ ፡ ዕድል ፡ የሚቆይበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይወሰን ፡ ውጤቱ ፡ ግን ፡ በልማት ላይ ፡ በዋለው ፡ ካፒታል ፡ ብዛት ፡ ይወሰናል ፡" ይላል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ኩባንያው ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋለውን ፡ ካፒታል ፡ መልሶ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ እንዲከፍል ፡ አይጠየቅም ። እንዲህ ፡ ማድረግም ፡ በመቋቋሚያ ፡ ዘመናት ፡ ትርፍ ፡ አጥቶ ፡ የነበረውን ፡ ድርጅት ፡ ይረዳል ፤ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ የማይችል ፡ ድርጅት ፡ ፈጽሞ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ። ሌላ ፡ ጥቅም ፡ መስጠትም ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ፤ ግን ፡ "የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ድርጅት ፡ ማሚያ ፡ (ሰብስዲ) ፡ የሚሰጥበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አይታይም ።"

## መደምደሚያ ፡

የውጭ ፡ ባለካፒታሎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉ ፡ ለማበረታታት ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አዋጅ ፡ የተጠበቀውን ፡ ያህል ፡ ውጤት ፡ ማስገኘቱ ፡ ያጠራጥራል ። እንዲያውም ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረጉ ፡ የውጭ ፡ ካፒታል ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ለመሳብ ፡ ለመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጠቃሚ ፡ ዘዴ ፡ መስሎ ፡ ከታያቸው ፡ ጉዳት ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ ሌላ ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ እንዳይፈጥሩ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረጉ ፡ የሚያደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ ከሚያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ ይበልጥ ፡ ይሆናል ። እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ በቀጥታ ፡ ከመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የሚወጣ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ኪሣራ ፡ በቀላሉ ፡ ሳይታሰብበት ፡ ይታለፍ ፡ ይሆናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃነት ፡ የውጭ ፡ ባለካፒታሎች ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ካፒታላቸውን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉ ፡ ማበረታታቱ ፡ አይቀርም ። ሌሎች ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ ካላቆሙ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ እንዲኖር ፡ ማስፈለጉ ፡ አይጠረጠርም ።

ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ ካፒታል ፡ ለመሳብ ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ማድረግ ፡ ይረዳል ፡ የሚል ፡ ኃይለኛ ፡ እምነት ፡ አላቸው ። ሌሎች ፡ ታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ይህንን ፡ ዘዴ ፡ እስከተከተሉ ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያም ፡ አብነታቸውን ፡ ለመከተል ፡ ተገደዳለች ።

---

58 ቴይለር ፤ ገጽ ፡ ፶፰ ።